# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም:-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 25 ሜትር ባንድ
**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**ታኅሣሥ 14 ቀን 2004 ዓ.ም**

**የወያኔ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ድንገተኛና አስቸኳዋይ ስብሰባ አደረገ፤**

**የቡና ላኪ ባለሀብቶች ለወያኔ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ በመስጠታቸው ተጥሎ የነበረው ገደብ ተነሳላቸው፤**

**በአቡዋሬ በአንድ ሳምንት ሁለት ግዜ ከ60 በላይ ሱቆች ጋዩ፤**

**የሐመር ብሔር በወያኔ ላይ አመፀ፤**

የወያኔ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ባልተሙዋላበት ሁኔታ ድንገተኛ አስቸኩዋይ ስብሰባ ማድረጉ ታወቀ:: በህዝቡ ዝምታ የተደናገጡት እነ መለስ ዜናዊ ባልተለመደ ሁኔታ ድንገት ማክሰኞ ታህሳስ 10 ቀን 2004 ዓ.ም ለግማሽ ቀን የፈጀ ምስጢራዊ ስብሰባ በቤተ መንግስት ማድረጋቸው ታውቆዋል::

እስከ ዛሬ ድረስ መደበኛ ስብሰባ ሲያደርጉ ቅዳሜና እሁድ ቀን የነበረ ሲሆን የአሁኑ ግን አስቸኩዋይ በመሆኑ ሁሉም የስራ አስፈጻሚ ባልተገኙበት እና ባልተሙዋሉበት ድንገት ማክሰኞ ዕለት ማድረጋቸው ታውቆዋል::

ሳይታሰብ እና ወቅቱን ሳይጠብቅ በመለስ ድንገት የተጠራው ይሄው ስብሰባ ላይ የተገኙት የወያኔ ቡድን ባለስልጣናት በየመሽታ ቤቱ ውስኪያቸውን ሲጋቱ አድረው የመጡ መሆኑን የጠቆሙት ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ የሚጠጣ ውሀ ለማቅረብ እንኩዋን የአፋቸው ጠረን አላስጠጋ ብሎ እጅግ አስቸጋሪ እንደነበርም ምንጮቹ ሳይጠቁሙ አላለፉም::

ድንገት የተጠራው ይሄው አስቸኩዋይ ስብሰባ በአሁኑ ሰዓት ህዝቡ አንዳችም ተቃውሞ አለማሰማቱና አለመተንፈሱ ያስደነገጠው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ መፍትሔ ይዘው ይመጣሉ በሚል የተጠራ ቢሆንም የተባሉትን ከመስማት በስተቀር አንዳችም ሀሳብ ሳይሰነዝሩ አድምጠው የተበተኑ በመሆኑ በተለመደው ማስፈራሪያ እና ዛቻ በባለስልጣናቱ ላይ ሲደነፋባቸው እንደዋለም ምንጮቹ ጠቁመዋል::

ዛሬ የኑሮ ውድነቱ እየናረ ከህዝቡ አቅም በላይ በሆነበት ወቅት ይባስ ብሎ ሰሞኑን በዓለም ላይ የነዳጅ ዋጋ እያሽቆለቆለ ባለበት በዚህ ግዜ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ መደረጉን ተከትሎ የበለጠ የእህልና ጥራጥሬ ብሎም ሸቀጦች ዋጋ እንዲንር በማድረጉ የተነሳ ህዝቡ ተቃውሞ ሊያሰማ ይችላል ተብሎ ቢጠበቅም ዝም በማለቱ የተደናገጠው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ቀኝ እጆቼ ናቸው የሚላቸውን የስራ አስፈጻሚ ኮሚቲ አባላትን ሰበስቦ ቢያናግርም አንዳችም መፍትሔ ሳያገኝ መቅረቱም ታውቆዋል::

ለግማሽ ቀን ያህል በተደረገው በዚሁ ስብሰባ ላይ ባለስልጣናቱ ሀሳብ እንዲሰነዝሩ ቢወተውትም ከምክትሉ ኃይለማርያም ደሳለኝ በስተቀር ሌሎች አንዳችም ትንፍሽ ሳይሉ በመቅረታቸው የተበሳጨው መለስ የኪራይ ሰብሳቢነትን ባህሪይ እየተላበሳችሁ ስለሆነ በዚህም ጉዳይ ላይ ወደፊት እንመክርበታለን ሲላቸው እንደነበረም ምንጮቹ ጠቁመውል::

ከእግር እስከ ጥፍራቸው በሙስና ተነክረውበት ያሉት እነ መለስ ዜናዊ ጣቶቹን ወደ ሌሎች ላይ እንዳይቀስር እሱም በሚስቱ እያግበሰበሰ መሆኑን ስለሚያውቁ ሊያዋርዱኝ ይችላል በሚል እስከ ዛሬ እያድበሰበሰ በዝምታ ሲያልፍ የነበረ ቢሆንም በማክሰኞው ስበሰባ ላይ ግን በሙስና እየተተበተባችሁ መሆኑን በተለያየ መልኩ ደርሶናል ጉዳዩን እስክናጣራ ድረስ ነው ዝም ያልናችሁ በማለትም ሲያስፈራራቸው እንደነበረም የውስጥ አዋቂዎቹ ጥቆማ አጋልጦዋል::

ከዚህ በፊት የብአዴኑ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባልና የወያኔው የግብርና ሚኒስትር ደርበው የተባለው ወጣት ካድሬ እንደ አሁኑ አስቸኳዋይ ስብሰባ ተጠርተው በሚነጋገሩበት ወቅት «ህዝቡ የሚጠይቀንን ጥያቄ መመለስ አልቻልንም..... መጀመሪያ በዚህ ጉዳይ ላይ መምከርና መወሰን አለብን..... ሌላው ችግር ተራ ነው» በማለት መለስ ያቀረበውን አጀንዳ በማጣጣሉ ከፍተኛ ሙግት ተነስቶ የነበረ መሆኑን ያስታወሱት ምንጮቹ ከዛን ግዜ ጀምሮ ስብሰባ ላይ እንዳይገኝ መለስ በምስጢር ያገደው ሲሆን ዛሬም ሌሎቹ ባለስልጣናት የሆዳቸውን አውጥተው እንዳይናገሩ ተመሳሳይ እጣ ፈንታ ይደርስብናል በሚል ፍርሀት ዝምታ ቢመርጡም መለስ ግን ሙሰኞች ናችሁ እያለ ሲዘልፋቸው እንደዋለም ከምንጮቹ ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል::

የህዝቡን ጥያቄ እንመለስ ብሎ መለስን የስንግ ይዞ ሲሞግተው የነበረው ይሄው የብአዴኑ ወጣት የግብርና ሚኒስትር ከዛን ግዜ ጀምሮ በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ ያልተገኘ ከመሆኑም በተጨማሪ በቢሮው ውስጥ ብቻ ተወስኖ እንዲቀመጥ ተደርጎ እንደሚገኝም የምንጮቹ ጥቆማ ያብራራል::

በዚሁ ድንገት በተጠራ ስብሰባ ላይ ስራ አስፈጻሚ የተባሉት ባለስልጣናት በሊዝ አዋጁ ላይም የራሳቸውን አቋዋም እንዲናገሩና አስተያየት እንዲሰጡ መለስ እና ኃይለማርያም ሲወተውቱ አንዳችም አስተያየት ሳይሰጡ ቢቀሩም ዋነኛውና ቀንደኛው የወያኔ ተዋናይ በረከት ስምኦን ግን ካድሬዎቹን እያብጠለጠለ ከተቃዋሚዎች ጋረ ግንኙነት አላችሁ ሲል በግድምድሞሽ ሲሰድባቸው እንደነበረም የምንጮቹ ጥቆማ አጋልጦዋል::

እስከ መጨረሻ ድረስ ትንፍሽ ያላሉት ባለስልጣናቱ በስብሰባው ማጠቃለያ ላይ በነበሩት አጀንዳዎች ላይ መስማማት አለመስማማታቸውን ተጠይቀው እንደሚስማሙ እጅ በማውጣት የገለጹ

መሆናቸውም የታወቀ ሲሆን ከስበሰባ ማብቂያ በሁዋላ እርስ በርስ በአይን እየተያዩ ሁሉም በሩጫ ወደ መኪኖቻቸው እንደሄዱም ምንጮቹ አብራርተዋል::

በተያያዘ ዜና በቡና ንግድ ላይ ተሰማርተው የነበሩት ባለሀብቶች ባለፈው ሳምንት የስራ ማቆም አድማ እንመታለን ብለው ማስጠንቀቂያ በመስጠታቸው የተደናገጡት እነ መለስ ዜናዊ የጣሉትን ማዕቀብ አነሱ::

የቡና ላኪ ነጋዴዎች በሀገሪቱ ውስጥ የሚደረጉ ማንኛቸውም የገንዘብ ድጋፍ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ተሳታፊ ሆነን ሳለ ከዓለም አቀፍ አቅርቦት ውጭ በኮንቲነር እንዲሆን መወሰኑ ተገቢ ካለመሆኑም በላይ ለወደፊቱ የህልውናችን ጉዳይ አጠያያቂ በመሆኑ ስራውን እናቆማለን በማለት በተወካዮቻቸው አማካኝነት ለመለስ ዜናዊ ደብዳቤ በመላካቸው የተጣለው እገዳ መነሳቱም ታውቆዋል::

ያለ በቂ ጥናት እና ውይይት እንዲሁም ያለ ባለሙያ ምክር ልገሳ ጥቂት የስርዓቱ አለቅላቂዎች ብቻ ባናፈሱት መንገድ እየተከተለ በመጉዋዝ ላይ ያለው የወያኔ ቡድን በየጊዜው ሽንፈቶች እየገጠሙት ሲሆን አሁንም በተመሳሳይ ቡና የሚላከው በኩንታል ሳይሆን በኮንቲነር ነው በሚል ያወጣውን መመሪያ በነጋዴው ህብረት ሳይወድ በግዱ ሊሻር መቻሉ ታውቆዋል::

በተለይ ነባር እና ከፍተኛ ሀብት አላቸው የተባሉት የቡና ላኪ ነጋዴዎች በብስጭት ለእረፍት በሚል ወደ ስዊዘርላንድ በመውጣታቸውና ከውጭ የቡና ተረካቢ ድርጅቶች እና ባለሀብቶች ጋር በመገናኘታቸው የተደናገጡት እነ መለስ ዜናዊ ነገሩ ስር ሳይሰድ ቶሎ ብለው መመሪያውን የሻሩ ሲሆን አሁንም ችግሩ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር ባለስልጣናት የሰሩት ስህተት ነው ሲል ለነጋዴዎቹ እንደተናገረም ለማወቅ ተችሎዋል::

የወያኔዋ ዋነኛ ሰላይ እና የቡና ላኪዎች ፕሬዝዳንት የሆነችው ዶክተር እሌኒ የተባለችው ግለሰብ ነባር እና ሀብታም የቡና ላኪ ነጋዴዎችን እያስፈራራች ወደ ውጭ የሚልኩትን በሙሉ እስዋ ባቁዋቁዋመችው ድርጅት ስር ብቻ እንዲያልፍ ብላ ለዓመታት ስትዳክር የነበረ ቢሆንም ያሰበችው ሳይሳካላት በመቅረትዋ ቁጥራቸው የበዙ የቡና ላኪ ባለሀብቶችን በተለያዩ ሰበቦች ለእስራት እንዲዳረጉ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረገች መሆኑም ታውቆዋል::

ይህችው የወያኔ ሰላይ የሆነችው እሌኒ የተባለችው ግለሰብ በተደጋጋሚ ግዜ ነጋዴዎቹን ወደ ሀገር ውስጥ ገበያ ቡናን እንዳያቀርቡ በመከልከልዋ በአሁኑ ሰዓት የአንድ ኪሎ ቡና ዋጋ አዲስ አበባ ላይ 150 ብር መድረሱን ለማወቅ ተችሎዋል::

በሀገር ውስጥ ገበያ ቡናን ስትሸጡ ነበር የተባሉ ነባር የቡና ነጋዴዎች በማጭበርበር በሚል በቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ ታስረው የሚገኙ ሲሆን ያሳሰረቻቸው እሌኒ የተባለችው መሆኑዋንም የእስረኛ ቤተሰቦች ሲናገሩ ተደምጠዋል::

ሰሞኑን ደግሞ የንግዱ ህብረተሰብ ባለው ወቅታዊ ሁኔታ ላይ ለመምከር በንግድ ምክር ቤት አዳራሽ የተገኘ ቢሆንም ሀሳቡ ተቀይሮ ዋነኛ አጀንዳ ሆኖ የዋለው የሊዝ አዋጁ መሆኑ ታወቀ::

በዚሁ ውይይት ላይ እንደተገለፀው ከሆነ በስብሰባ አዳራሹ ውስጥ የተገኙት ተሰብሳቢ የንግዱ ማህበረሰብ አባላት በሙሉ በአሁኑ ወቅት ፈታኝ እና አፋኝ የሆኑ ህጎች እየወጡ ህዝቦች በነፃነት ለመንቀሳቀስ እንዳይችሉ እየተደረገ በመሆኑ አስቸኳዋይ እርምት እንዲደረግበት በማለት ከፍተኛ ተቃውሞ ያሰሙ ሲሆን ያቀረቡትን ጥያቄና ያሰሙትን ተቃውሞ የሚመልስ አንድም ባለስልጣን አለመገኘቱም ታውቀዋል::

በዕለቱ በተያዘው አጀንዳ መሰረት የንግዱ ማህበረሰብ ከመንግስት ባለስልጣናት ጋር ለመምከር በሚል የተያዘ ቢሆንም የወያኔ ባለስልጣን የሆነው እስራኤል የተባለው ግለሰብ ሳይገኝ የቀረ መሆኑን የጠቆሙት የስብሰባው ተሳታፊዎች የንግዱ ህብረተሰብ ግን እርስ በርስ ሰፊ እና ጥልቅ ውይይት እና ምክክር ሲያደርጉ መዋላቸው ታውቀዋል::

ስብሰባውን ሲመሩ የነበሩት የኢትዮጵያ ንግድ ማህበራት ዘርፍ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት አቶ ኢየሱስወርቅ ዛፉ ሲሆኑ ከተሰብሳቢዎቹ የቀረቡትን ጥያቄና ሀሳብ ካደመጡ በሁዋላ እኔም በበኩሌ ብዙ ጥያቄዎች ነበሩኝ ይሁን እንጂ እኛን ፈርተው ይሁን ሳይመቻቸው የተላኩት ባለስልጣን ሳይመጡ ቀርተዋል ሲሉ ተሰብሳቢውን ፈገግ አሰኝተዋል::

የንግዱ ማህበረሰብ አባላት ይህን ውይይት ባደረጉ ጥቂት ቀናት ውስጥ የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት ለፕሬዝዳንትነት ባደረገው ምርጫ ብዙ እጩዎችን አወዳድሮ ለመጀመሪያ ግዜ ሴት ፕሬዝዳንት የመረጠ ሲሆን እኚህ ሴት በ60ዎቹ በነበረው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ተሳትፎ የነበራቸው እንደነበሩም ቅርበት ካላቸው ወገኖች የተገኘው ጥቆማ አስረድቶዋል::

ወ/ሮ ሙሉ ታፈሰ የተባሉት እኚሁ ነባር የንግድ ምክር ቤት አባል በተለያዩ ግዜ የተለያዩ ይዘት ያላቸውን መጻህፍቶች አሳትመው ለንባብ ያበቁ ከመሆናቸውም በላይ በሴቶች ዙሪያ ሰፊ ተሳትፎ ሲያደርጉ የነበሩና ከወያኔ ጋር ግጭት ሲፈጥሩ የነበሩ መሆናቸውንም ቅርበት ካላቸው ወገኖች ገለፃ ለማወቅ ተችሎዋል::

ወያኔ በነጋዴዎች ላይ ካለው ጥላቻ የተነሳ የተለያዩ ሰንካላ ምክንያቶችን እየደረደረ ገሚሱን ለእስር ሌሎቹንም ከስራ እያፈናቀለ የሚገኝ ሲሆን ሰሞኑን ደግሞ ሱቆቻቸውን እያቃጠለ ባዶ እጃቸውን ቀርተው ለልመና እየዳረጋቸው መሆኑ ታውቆዋል::

አቡዋሬ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ከትናንት በስቲያ በደረሰ የእሳት አደጋ ከ60 በላይ ሱቆች ሙሉ ለሙሉ የጋዩ ሲሆን 10 ያህል መኖሪያ ቤቶችም አብረው እንዲጋዩ መደረጉን ከተቃጠለባቸው ሰዎች የተገኘው ጥቆማ ያስረዳል::

አራት ኪሎ ቤተ መንግስት አቅራቢያ የሚገኘው ይሄው የገበያ ማዕከል ዝቅተኛውን ማህበረሰብ በተመጣጣኝ ዋጋ ሲያስተናግድ የኖረ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን የወያኔ ቡድን በሊዝ ለባለሀብት ሸጦ ጠቀም ያለ ገንዘብ ለማግኘት ሲል እና የቤተ መንግስቱን ውበት ያበላሻሉ በሚሉ

ምክንያቶች ሌሊት በእሳት ለኩሶ ዙሪያውን በፌዴራል ፖሊስ ከብቦ ሁሉም እንዲወድም ማድረጉን ሱቃቻቸው የተቃጠለባቸው ሰዎች እያነቡ ይገልጻሉ፡፡

ቃጠሎው ከመከሰቱ ጥቂት ቀደም ብሎ ማንነቱ ያልታወቀ ሰው በየሱቆቹ በር ላይ እየዞረ እሳት ተነሳ ውጡ! እሳት ተነሳ ውጡ! በሚል ከሱቆቻቸው እንዲወጡ እንዳደረጋቸውና እነሱ ከወጡ በሁዋላ እሳት መነሳቱን ያጋለጡት ነጋዴዎቹ ንብረቶቻቸውን ለማትረፍ ቢሞክሩም እንዳይጠጉ መከልከላቸውን ሱቆቻቸው የተቃጠለባቸው ሰዎች እያለቀሱ ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡

ከዚህ በፊት ከዚህ ቦታ ላይ ትነሳላችሁ ስንባል መተኪያ ቦታ ስጡን እና እንነሳለን በማለት ሞግተናቸው ነበረ ያሉት እነዚሁ የእሳቱ ሰለባ የሆኑት ዜጎች የእኛን ሙግት እንደ ንቀት ቆጥረውት እነሆ ዛሬ አንዳችም ጥሪት ሳንይዝ ንብረቶቻችን በሙሉ እንዲወድምብን አድርገውናል ሲሉም በምሬት እና በሀዘን እየገለጹ ይገኛሉ፡፡

በአንድ ሳምንት ሁለት ቃጠሎ ያስተናገደው አቡዋሬ ከአንድ ሳምንት በፊትም በዚሁ ሰፈር በገደራ ሆቲል አቅራቢያ እሳት ተነስቶ ብዙ መኖሪያ ቤቶች እና ሱቆች መጋየታቸው አይዘነጋም፡፡

በመጨረሻም  የወያኔ ቡድን በደቡብ ክልል ውስጥ የሚገኙትን ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ትጥቅ ለማስፈታት ሙከራ አድርጎ ሳይሳካለት እንደቀረና ይህንኑ ተከትሎ በአካባቢው ውጥረት መንገሱን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገለፀ፡፡

ወያኔ በደቡብ ክልል ኦሞ ዞን የሚገኙ ህዝቦችን በተለይ የሀመር ብሔረሰብ ተወላጆችን መሳሪያ ለማስፈታት አንድ ሻለቃ ጦር ወደ ስፍራው ልኮ የነበረ ቢሆንም ሁሉም አሻፈረኝ በመለታቸው ሳይሳካለት ከመቅረቱም በተጨማሪ አንድም የወያኔ ካድሬ ወደ አካባቢው ከእንግዲህ ዝር እንዳይል መመሪያ መስጠታቸውን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልያዋል፡፡

የወያኔ ቡድን በኃይል አልሳካ ሲለው ሰሞኑን በሀገር ሽማግሌ እንዲያደራድሩት ሙከራ እያደረገ ቢሆንም ህዝቡ በተፈጸመባቸው ሸፍጥ በመበሳጨት እስከ ዛሬ ድረስ ያልተስማማ መሆኑን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል፡፡

በወያኔና በሐመር ብሔረሰቦች መሀከል በተፈጠረው ሽኩቻ ምክንያት ለምርምር እና ለጥናት ብለው ወደ አካባቢው የሚገቡ የውጭ ሀገር ዜጎች እና ኢዮጵያውያኖች በሐመሮች ጥብቅ ፍተሻ እና ጥበቃም እንደሚደረግባቸው ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል፡፡

ከእንግዲህ ወታደር ወደዚህ ዞን እንዳይመጣ ብለው አቁዋማቸውን የገለፁት የሀመር ብሔረሰቦች ከተማ ያሉ ዘመዶቻቸውን ወያኔ እያፈላለገ በጥቅም ይዞ በሽምግልና ለመላክ እየተሩዋሩዋጠ መሆኑም ታውቆዋል፡፡

ባለፉት ሁለት ዓመታት በደቡብ ክልል በኦሞ ዞን በተከሰተ ድርቅ ብዙ ዜጎች እና ከብቶች የረገፉበት ሲሆን በተለይ የሀመር ብሄር ላይ የከፋ ችግር ደርሶ እርዳታ ሳይሰጣቸው

እንደቀረ ያስታወሰው የደረሰን ዘገባ ወያኔ ዛሬ በልማት ስም ለዘመናት ከኖሩበት እና እትብታቸው ከተቀበረበት ቀዬ ሊያፈናቅላቸው መሆኑን በመረዳታቸው ግጭት ሊፈጥሩ መቻላቸውን ዘገባው አስረድቶዋል፡፡

የወያኔ ቡድን የሐመር ብሄር ተወላጆችን መሳሪያቸውን አስቀድሞ አስፈትቶ እንዳሻው ለማድረግ አስቦ የነበረ ቢሆንም ሐመሮች ቀድመው ደባውን በማወቃቸው ትጥቅ አንፈታም በማለት አመጽ ያነሱ ከመሆኑም በተጨማሪ የወያኔ ጦር ወደ ስፍራው እንዳይገባ ብርቱ ማስጠንቀቂያ ማስተላለፋቸው ታውቆዋል፡፡

በጉዳዩ የተበሳጩት የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት ለአየር ኃይል መኮንኖች ትዕዛዝ በመስጠት በጦር ሄሊኮፕተር ያስፈራሩዋቸው መሆኑንም የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡